# **አለም አቀፍ ጥበቃ ለማግኘት ቃለ መጠይቅ (ኢንተርቪው)**

አለም አቀፍ ጥበቃ ለማግኘት ማመልከቻ ስላስገቡበት ምክንያት **ለቃለ መጠይቅ** እንዲመጡ እንጠራዎታለን ። ይህ በፖላንድ አለም አቀፍ ጥበቃ ለጥገኝነት የሚጥይቁት ሕገ መንግስት (ከሰኔ 13፤ 2003) መሰረት የረቀቀ ነው። ቃለ መጠይቁን የሚጠይቁት የጥገኝነት ሰርአት ክፍል በውጭ አገር ዜጋዎች ድርጅት ሰራተኞች ናቸው።

## **በቀሩበት ወቅት**

ወደ ቃለ መጠይቁ **ባይመጡ** እና ተገቢውን ምክንያት **በሰባት ቀን** ውስጥ ባያቀርቡ ያስገቡት ጉዳዩ ሙሉ በሙሉ ይሰረዛል (ጉዳዩ የህብረተሰብ ጥቅም የሚጻረር ካልሆነ) ። ተገቢ ምክንያት ካሎት በወረቀት በማስደገፍ ያስገቡ።

## **ሚስጢራዊ ጉዳይ**

በጉዳዩ ላይ ሁሉም የሚሰጡትን መረጃዎች **በሚስጢር መያዝ** አለባቸው እና በፖላንድም ሕግ **የተጠበቁ** ናቸው። እርስዎ በውጭ አገር ዜጋዎች ድርጅት የሚናገሩት መረጃ በሚስጢር ይቀበላል እና ለማንም አይነገርም (በተለይም እርስዎ የተወለዱበት አገር ባለስልጣናት)። ስለዚህ የርስዎ መረጃዎችን ለጥገኝነት ስርአት ክፍል ሰራተኛ ለመስጠት እንዳያቅማሙ።

## **ሃላፊነትዎ**

በቃለ መጠይቅ ጊዜ ሁሉም አለም አቀፍ ጥበቃ (ጥገኝነት) ለማግኘት የሚያስፈልጉትን መረጃዎች መስጠት ይገባዎታል። በትክክል **የተዘረዘሩትን መልሶች** ለመስጠት ይጠቅምዎታል። ሁሉም ሌላ መረጃዎች በተለይም የሰነድ መረጃ (ምስክር ወረቀቶች ፤ መታወቂያ ፤ ፔንድራይቭ ላይ ያለዎት መረጃ) በቃለ መጠይቅ ላይ የተናገሩት መረጃ ለማረጋገጥ የሚችሉ ከሆኑ ለማስገባት ሃላፊነት አለብዎ።

## **የቃለ መጠይቅ እና ሌላ መረጃዎች ጥቅም**

በቃለ መጠይቅ ጊዜ የተናገሩት መረጃ በተጨማሪም የሰጡት ሌላ መረጃዎች ሁሉም በጣም ትልቅ አስፈላጊነት ስላላቸው አለም አቀፍ ጥበቃ ለማግኘት ከፍተኛ ጥቃሚነት ይኖራቸዋል። በነሱ መስሰረት ውሳኔ ይወሰናል። አንድ ወሳኙ ነገር ካልተናገሩ ወይንም የውሸት መረጃ የሚስጡት ከሆነ ለጉዳይዎት ጥሩ ምላሽ አያገኙም።

**ከቃለ መጥይቁ በሀዋላ**

ከቃለ መጠይቁ በሀዋላ **አዲስ ወሳኝ** መረጃ ከተገኘ **ወዲያውኑም** የጥገኝነት ስርአት ክፍል ግንኙነት ያድርጉ። ተጨማሪ ቃለ መተይቅ ለማድረግ ወይንም አዲስ ምስክር ለመጠየቅ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ ። በዚህ ማመልከቻ ላይ የምስክሩ ስም ከነ አባቱ ስም እና አድራሻ መስጠት ይጠበቅብዎታል። እንዲሁም ምን አይነት ማስረጃ እንዳለው ማመልከት ያስፈልጋል።

አዲስ መረጃዎች ፤ ምስክር ወረቀቶች ወይም ማመልከቻዎች፡

➔በፖስታ መላክ ይቻላል ፤ አድራሻው - ul. Taborowa 33, 02-699 Warszawa

ውይንም

➔በፋክስ መላክ ይቻላል ፤ የፋክስ ቁጥር 0-22-601-51-23

ወይንም ደግሞ

➔በአካልም ማስገባት ይቻላል ፤ አድራሻው - ul. Taborowa 33, Warszawa

**አድራሻዎትን ቢቀይሩም**

**ሁልጊዜ** አድራሻዎን ሲቀይሩ ማሳወቅ አለብዎት። ስለ አዲስ አድራሽ ባያሳውቁ ሁሉም ወደ አሮጌ አድራሻ የተላኩት ደብዳቤዎች **እንደደረሰዎት** ይቆጠራል።

**ውሳኔ**

አለም አቀፍ ጥበቃ ለማግኘት ማመልከቻዎ ከማየታችን በሀዋላ **ውሳኔ በጽሑፍ** እንሰጣለን። ውሳኔው ወደሰጡት አድራሻ ወይም ወኪል ካለዎት ወደ ወኪል አድራሻ እንልካለን። እርስዎ እና ሌላ ሰው ሁሉ በውሳኔው ውስጥ የተጠቃለለ ውሳኔውን መጠበቅ አለባችሁ። በውሳኔው ውስጥ በሚገባዎት ቋንቋ የሚቀጥሉትን መረጃዎች ያገኛሉ፡

➔የጉዳዩ **ውጤት** እና የውሳኔው ሕጋዊ መሰረት

➔በውሳኔ ካልተስማሙም **ስለቅሬታ** ምርጫ